# ድጎማ የሚያስገኝ የመልስ ጉዞ ወደ ኢትዮጵያ

በኖርዌይ አገር የመኖሪያ ፈቃድ ከሌለህ/ሽ የግዴታ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ አለብህ/ሽ። ወደ አገርህ ለመመለስ እና እዚያ አዲስ ሕይወት ለመጀመር እገዛ እንዲደረግልህ መጠየቅ ትችላለህ።

## ለመልስ ጉዞው ማመልከት የምትችለው/ይው

- በፖለቲካ ጥገኝነት ጥበቃ እንዲደረግልህ/ሽ፣ወይም የመኖሪያ ፈቃድ እንዲሰጥህ/ሽ አመልክተህ/ሽ የዕምቢታ መልስ ተሰጥቶህ/ሽ እንደሆነ
- ለማመልከቻህ/ሽ መልስ በመጠበቅ ላይ የምትገኝ/ኚ ከሆነ
- በኖርዌይ አገር እየኖርክ ያለኸው/ሽው ያለ ሕጋዊ መኖሪያ ፈቃድ ከሆነ

ነው፣

## የምታገኘው/ኚው

- የኢኮኖሚ እና የተግባር እገዛ፣
- የመጓጓዥያ ሰነድ ወይም ፓስፖርት በማውጣት በኩል የሚደረግ እገዛ፣
- ወደ ኢትዮጵያ የሚያደርስ የአውሮፕላን ቲኬት፣
- በኖርዌይ አገር ከዓለም አቀፉ የስደተኞች ዝውውር ድርጅት (IOM)፣በኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ ከ የስደተኞች እና ከስደት ተመላሾች ሚንስቴር መ/ቤት (ARRA) የሚሰጥ የምክር አገልግሎት፣

## ምን ዓይነት የኢኮኖሚ እገዛ ነው የምታገኘው/ኚው?

- ኢትዮጵያ እንደደረስክ/ሽ ከ IOM በጥሬ ገንዘብ 15 000 ክሮነር ይሰጥኻል/ሻል፣
- በ ARRA በኩል ለሥራ ማፈላለጊያ፣ ለሥልጠና፣ የግል ሥራ ለመጀመር፣ለት/ቤት ወይም ለትምህርት ወደ 30 000 ክሮነር የሚጠጋ እገዛ ይደረግልኻል/ሻል፣

የመልስ ጉዞውን የሚያደርጉ ወላጆች ለእያንዳንዱ አብሯቸው ለሚመለስ ልጅ የ 10 000 ክሮነር እገዛ ይሰጣቸዋል።

## በሚከተለው ሁኔታ ነው እገዛውን የምትጠይቀው

በ ስልክ ቁጥር 800 37 404 (800 FRIVILLIGRETUR (በፈቃደኝነት የሚደረግ የመልስ ጉዞ) ለ IOM በመደወል፣

በ iomoslo@iom.int የኢሜይል አድራሻ መልዕክት በመላክ፣

የማመልከቻ ቅጹን በ www.iom.no ድረ ገጽ ላይ ታገኛላችሁ።

UDI